በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ

# የዘር አምራችና ግብይት ኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀትና አሰራር **መመሪያ**

መመሪያ ቁጥር-----------------

(ረቂቅ)

አዲስ አበባ

ታህሳስ 2009 ዓ.ም

መግቢያ

አገራዊ የሆነ ምርትና ምርታማነትን በመጨመር የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥና የውጭ ንግድ ተሳታፊነት ለማሳደግ የተሻሻሉ የእጽዋት ዝርያዎች የሚጫወቱት ፋይዳ ከፍተኛ ነው፡፡ ይህን እውን ለማድረግ ደግሞ በምርምር ተሻሽለው የሚወጡትን ዝርያዎች በጥራትና በከፍተኛ መጠን ለተጠቃሚው ተደራሽ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የዘርን ተደራሽነት ለማረጋገጥ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ባለድርሻ አካላት ልዩ ልዩ አማራጮችን ሲከተሉ ቆይተዋል፡፡ በፌደራልና በክልል መንግስታት ከፍተኛ ትኩረት እያገኙ ከመጡት አማራጮች ዋናው ደግሞ የዘር አምራች ህብረት ሥራማህበራት አቅም በማሳደግ ዘር አቅርቦትን በዓይነት በጥራትና በመጠን ማሳደግ ነው፡፡ ይህን የመንግስት የፖሊሲ አቅጣጫ በመከተል በአሁኑ ሰዓት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የዘር አምራች መሰረታዊ ህብረት ሥራ ማህበራትና ዩኒየኖች ተደራጅተዋል፡፡ እነዚህን እና ከዚህም በኃላ የሚቋቋሙትን ዘር አምራች እና ግብይት ህብረትሥራ ማህበራትን አደረጃጀትና አሰራራቸው የሀገሪቱን የህብረት ስራ እና  የዕጽዋት ዘር ህጎች መሰረት  ባደረገ መልኩ መምራት ያስፈልጋል፡፡

ስለዚህም ሀገሪቱ በምትከተለው የግብርና መር ኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ መሰረትምርትና ምርታማነት የሚያሳድጉ፣የምግብ ዋስትናን የሚያረጋግጡና የውጭ ንግድን የሚያጎለብቱ ዝርያዎች የሚጠይቁትን የጥራት ቁጥጥር መስፈርት ጠብቀው በከፍተኛ መጠንና ጥራት እንዲመረቱ፣ የተጠቃሚዎች የምርጥ ዘር ተደራሽነት፣ የአባላትን ባለቤትነት፣ተቆጣጣሪትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የዘር አምራች ኅብረት ስራ ማህበራት  አደረጃጀትና አሰራርን የሚደግፍ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለዚህ የኅብረት ስራ ኤጀንሲ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ  መንግስት አዋጅ ቁጥር -------------በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. አውጭው ባለስልጣን

የኅብረት ሥራ አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ ፺፯ ንዑስ አንቀጽ ፫ እና በደንብ ቁጥር ------------------የተደነገገውን ለማስፈፀም ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

2. አጭር ርእስ

ይህ መመሪያ የዘር አምራችና ግብይት ኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀትና አሰራር ረቂቅ መመሪያ ቁጥር --------- ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

3. ትርጓሜ

በኅብረት ሥራ አዋጅ ቁጥር 985/2009 እና በእጽዋት ዘር አዋጅ ቁጥር 782/2005 የተሰጡ ትርጉሞች እንደተጠበቁ ሆኖ የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር በዚህ መመሪያ መሰረት

3.1. "አዋጅ" ማለት የህብረት ሥራ አዋጅ ቁጥር 985/2009 እና የእጽዋት ዘር አዋጅ ቁጥር 782/2005 ናቸው፡፡

3.2. "አግባብነት ያለው ባለሥልጣን" ማለት በኅብረት ሥራ እና በዕጽዋት ዘር አዋጆች መሰረት የፌደራልና የክልል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲዎችንና የፌደራልና የክልል ዘር ጥራት ለመቆጣጣር ሥልጣን የተሰጣቸው ተቋማት ያመለክታል፡፡

3.3. "የዘር አምራች እና ግብይት ኅብረት ሥራ ማህበራት"ማለት በኅብረት ሥራ አዋጅ መሰረት ተመዝግበው በዩኒየን ወይም በሌላ የዘር ኩባንያ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መሰረት ጥሬ ዘር አምርተው የሚያስረክቡ ወይም የራሳቸው የብቃት ማረጋገጫ አግኝተው ዘር አምርተው አዘጋጅተው ለገበያ የሚያቀርቡ ናቸው፡፡

3.4. "ኩታገጠም"ማለት በአንድ አካባቢ የሚገኙ አርሶአደሮች ስምምነት ፈጥረው ያላቸውን መሬት በአንድ ሰብል እንዲሸፈን በማድረግ ዘር የሚያመርቱበት ማሣ ማለት ነው፤

3.5. "የኮንትራት ዘር አምራቾች(outgrower)" አግባብ ባለው የዘር ጥራት ተቆጣጣሪ ባለስልጣን የብቃት ማረጋገጫ ላገኘ ኅብረት ስራ ዩኒየን ወይም የዘር ኩባንያ በውል መሰረት ጥሬ ዘር አምርተው የሚያስረክቡ የዘር አምራች እና ግብይት ኅብረት ሥራ ማህበራት ናቸው፡፡

4. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ዘር አምርተው ለገበያ በሚያቀርቡ፣ በኅብረት ሥራ አዋጅ ቁጥር 985/2009 መሰረት በተመዘገቡና በዕጽዋት ዘር አዋጅ ቁጥር 782/2005 መሰረት አግባብነት ባለው የዘር ጥራት ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ባገኙት ኅብረት ሥራ ማህበራት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

5. የመመሪያው ዓላማ

፩/ ጥራቱን የጠበቀ ዘር ለአርሶ አሮች፣ከፊል አርብቶ አደሮችና ሌሎች የዘር ተጠቃሚዎች በመጠን፣ በዓይነትና በተወዳዳሪ ዋጋ ተደራሽ ማድረግ የሚችሉ ብቃትና ዘላቂነት ያላቸው የዘር አምራች ኅብረት ሥራ ማህበራት ለመፍጠር የሚደረገውን ጥረት ለማገዝ፣

፪/ የዘር አምራችና ግብይት ኅብረት ሥራ ማህበራት በዘር ማምረትና ግብይት ረገድ የሚያጋጥማቸውን የአደረጃጀትና የአሰራር ችግር ለመፍታት የሚደረገውን ጥረት ማገዝ፣

፫/ አስተማማኝ ገበያ በመፍጠር ዘር አምራች አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ ማድረግ፣

፬/ የባለድርሻ አካላትን ሚና በማሳለጥ ለዘር አምራችና ግብይት ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚደረገውን ድጋፍ ማጎልበት፣

6. የኅብረት ሥራ ማህበራት መሠረታዊ መርሆዎች

6.1.የኅብረት ሥራ ማኅበራት አባልነት በማኅበራቱ አገልግሎት ለመጠቀም ለሚፈልጉና የአባልነት ግዴታዎችን ለመቀበል ፈቃደኛ ለሆኑ ሰዎች ሁሉ በጾታ፣ በማኅበራዊ አቋም፣ በዘር፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በአካል ጉዳተኝነት ወይም በሃይማኖት ልዩነት ሳይደረግ ለሁሉም ክፍት ይሆናል፡፡

6.2.የኅብረት ሥራ ማኅበራት ፖሊሲ በማውጣትና ውሳኔዎችን በማስተላለፍ የነቃ ተሳትፎ በሚያደርጉ አባላት የሚመሩ ዲሞክራሲያዊ ድርጅቶች፣ እያንዳንዱ አባል እኩል ድምጽ ያለው እንዲሁም አንድ አባል አንድ ድምጽ ብቻ ያለው ይሆናል፡፡

6.3.ከትርፍ ላይ ለመጠባበቂያ እና ለሌሎች አገልግሎቶች ተቀንሶ ከተቀመጠ በኋላ አባላት ከኅብረት ሥራ ማህበሩ በገዙት ዕጣ መጠን እና ባደረጉት ተሣትፎ መሠረት ቀሪው ትርፍ ይከፋፈላል፡፡

6.4.ኅብረት ሥራ ማኅበራት ከሌሎች አካላት ጋር መንግሥትንም ጨምሮ ስምምነት የሚያደርጉት ወይም ከኅብረት ሥራ ማኅበራቸው ውጭ ከሚገኝ ምንጭ ገንዘብ በመበደር ካፒታላቸውን ማሳደግ የሚችሉት የአባላት ዲሞክራሲያዊ ቁጥጥርን በሚያረጋግጥ፣ የኅብረት ሥራ ማኅበራቸውን የራስ በራስ ማስተዳዳር መብት በሚጠብቅ እንዲሁም የራስ አገዝ ባህሪውን በማይነካ ሁኔታ መሆን ይኖርበታል፡፡

6.5.የኅብረት ሥራ ማኅበራት አባላት፣ ተመራጮች፣ ሥራ አስኪያጅ እና ሠራተኞች ለኅብረት ሥራ ማኅበራቸው ዕድገት ተገቢውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ትምህርትና ሥልጠና እንዲያገኙ ያደርጋሉ፤ ስለ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ምንነትና ጥቅም ለሕዝቡ በተለይም ለወጣቱ ያስተዋውቃሉ፡፡

6.6. በአካባቢ፣ በሀገር አቀፍ፣ በአህጉር አቀፍ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚገኙ የኅብረት ሥራ ማህበራት መዋቅሮች ጋር በመተባበር የኅብረት ሥራ ማህበራት እንቅስቃሴን በማጠናከር አባሎቻቸውን በሚገባ ያገለግላሉ፡፡

6.7. የኅብረት ሥራ ማኅበር አባሎቻቸው ባፀደቋቸው ፖሊሲች አማካይነት በአካባቢያቸው ላለው ኅብረተሰብ ዘላቂ ልማት ለማምጣት የሚያስችል ተግባር ያከናውናሉ፡፡

7. የኅብረት ሥራ ማህበራት እና የአባላት እሴቶች

7.1. የኅብረት ሥራ ማህበራት እሴቶች፣

7.1.1. ራስን በራስ መርዳት፣

7.1.2. የግል ሃላፊነትን መወጣት፣

7.1.3. ዴሞክራሲን ማስፋፋት፣

7.1.4. እኩልነት፣

7.1.5. ፍትሃዊነት፣

7.1.6. ወንድማማችነት፣ይሆናሉ፡፡

7.2. ፤የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት የሥነ-ምግባር እሴቶች፣

7.2.1. ታማኝነት፣

7.2.2. ግልፀኝነት፣

7.2.3. ማህበራዊ ኃላፊነት፣

7.2.4. ለሌሎች ማሰብ፣ይሆናሉ፡፡

ክፍል ፪

የዘር አምራች እና ግብይት ኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት

**የዘር አምራች እና ግብይት ኅብረት ሥራ ማህበራት አመሰራረት**

8. የዘር አምራች እና ግብይት ኅብረት ሥራ ማህበራት አመሰራረት ከመሰረታዊ እስከ ፌደሬሽን ሆኖ በኅብረት ሥራ አዋጅ ቁጥር 985/2009፣ በዕጽዋት ዘር አዋጅ ቁጥር 782/2005 እና አነዚህን ለማስፈጸም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

9. ዘር ማምረትና ግብይት መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማሕበራት መነሻ አባላት ቁጥር

9.1. የመስክ ሰብሎች ዘር ማምረት ሥራ ከሆነ ከ50 ማነስ የለበትም፡፡

9.2. ለአትክልት፣ፍራፍሬና መኖ ዘር ማምረት ከሆነ ከ15 ማነስ የለበትም፡፡

10. ከመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር በላይ ለሆነ አደረጃጀት ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ኅብረት ሥራ ማህበራት ሆነው ሊመሰርቱ ይችላሉ፡፡

## የዘር አምራች እና ግብይት ኅብረት ሥራ ማህበራት አባልነትን በተመለከተ

11. ማንኛውም ሰው የመሰረታዊ ዘር አምራች እና ግብይት ኅብረት ሥራ ማህበር አባል ለመሆን
    11.1. በኅብረት ሥራ አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ ፪ እና ፫ የተመለከቱትን እና አዋጁን ለማስፈጸም የወጡት ደንብ ላይ ስለ ኅብረት ሥራ ማህበር አባል መሆን የተጠቀሱት መስፈርቶች እደተጠበቀ ሆኖ
    11.2. ለመሰረታዊ ዘር አምራች እና ግብይት ኅብረት ሥራ ማህበር አባል ለመሆን
        11.2.1. የዘር ጥራት ተቆጣጣሪው አካል ያወጣውን የማሳ ጥራት መስፈርት የሚያሟላ የግሉ የእርሻ መሬት ያለው ወይም በኪራይ ስለማግኘቱ የመሬት ኪራይ ውል ማስረጃ የሚያቀርብ፤
        11.2.2. የእርሻ ማሳውን ኩታገጠም ለማድረግ አመቺ የሆነና የኅብረት ሥራ ማሕበሩ በሚያቅደው መሰረት የተፈለገውን ዘር እና ዝርያ የሚያመርት፤
        11.2.3. ማህበሩ በሚያዘጋጀው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የቅድመ እና ድህረ-ምርት የእርሻ ተግባራትን የሚፈጽም፤
        11.2.4. ማሳውን አግባብ ላለው የመስክ ዘር ጥራት ተቆጣጣሪ ባለሙያ የሚያስፈትሽ፤
        11.2.5. ከኅብረት ሥራ ማሕበሩ ጋር በገባው የግዥ ውል መሰረት ያመረተውን ዘር ከአውድማ ወደ ኅብረት ሥራ ማህበሩ በቀጥታ የሚያስረክብ፤
    11.3. ከመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር በላይ ለሆነ አደረጃጀት(ዩኒየን ወይም ፌዴሬሽን
        11.3.1. አግባብ ባለው የዘር ተቆጣጣሪ ባለስልጣን የሚጠየቀውን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እና የአደራጅ ባለስልጣኑን መስፈርቶች አሟልቶ የተመዘገበ
        11.3.2. ከዚህ መመሪያ በፊት ለተደራጁ ግን የዘር ጥራት ተቆጣጣሪ ባለስልጣን የሚጠየቀውን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያልነበራቸው ህብረት ሥራ ማህበራት በአውት ግረወር ፤ ወይም ራሳቸውን ችለው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ያወጣሉ።

### ክፍል ፫

### የዘር አምራች እና ግብይት ኅብረት ሥራ ማህበራት የሥራ ክልል

12. የዘር አምራች ኅብረት ሥራ ማህበራት የስራ ክልል
    12.1. በኅብረት ሥራ ማህበሩ የመተዳደሪያ ደንብ በሚወሰነው መሰረት ይሆናል።
    12.2. ኅብረት ሥራ ማህበሩ ምርትና አገልግሎቱን ተደራሽ ለማድረግ እንደ አስፈላጊነቱ ቅርጫፍ መክፈት ይችላል።
    12.3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ እንቀጽ 12.1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድ የሥራ ክልል ውስጥ ሌላ የዘር አምራች ኅብረት ሥራ ማህበር በተመሳሳይ የዕጽዋት ዘር ማምረት ሥራ ላይ መሰማራት አይችልም።

### ክፍል ፬

### የዘር አምራችና የግብይት ኅብረት ሥራ ማህበር ምዝገባ

13. ማንኛውም የዘር አምራችና የግብይት ኅብረት ሥራ ማህበር አግባብ ባለው ባለስልጣን ቀርቦ መመዝገብ አለበት።

14. በኀብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ 985/2009 አንቀጽ 9 የተጠቀሱ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው

14.1. ማንኛውም ኀብረት ሥራ ማኀበር፣ የኀብረት ሥራ ማኀበር ሆኖ ለመመዝገብ ማመልከቻውን ከሚከተሉት ጋር አያይዞ አግባብ ላለው ባለሥልጣን ያቀርባል፤

ሀ) የመሥራቾች ስብሰባ ቃለ ጉባኤ እና የአባላት ፊርማ

ለ) ማኀበሩን መተዳደሪያ ደንብ አንድ ዋና እና ሌሎች ሁለት ቅጂዎች፤

ሐ) የኀብረት ሥራ ማኀበሩን የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ስም፣ የሥራ ድርሻና ኃላፊነት፣ አድራሻና ፊርማ፤

መ) የኀብረት ሥራ ማህበሩን የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት ስም፣ የሥራ ድርሻና ኃላፊነት አድራሻና
ፊርማ፤

ሠ) የኀብረት ሥራ ማኀበሩ አባላት ሆነው የሚመዘገቡት ግለሰቦች አባል ለመሆን ብቁ መሆናቸውን የሚያስረዱ ዝርዝር ሁኔታዎች በኀብረት ሥራ ማኀበሩ መተዳደሪያ ደንብ
ውስጥ በግልፅ መቀመጥ ማረጋገጥ፣

ረ) የኀብረት ሥራ ማህበሩ ከመሠረታዊ ኀብረት ሥራ ማህበር በላይ ከሆነ አባል የሚሆኑ ኀብረት ሥራ ማህበራት ተመሳሳይ አላማ እና ተግባር እንዲሁም ፍላጎት ያላቸው፤

ሰ) የኀብረት ሥራ ማህበሩ ከመሠረታዊ ኀብረት ሥራ ማህበር በላይ ከሆነ የመስራች አባል ኀብረት ሥራ ማህበራቱን አድራሻ እና የተወካዮች ፊርማ መያዝ አለበት፤

ሽ) የኀብረት ሥራ ማህበሩን የሦስት አመት የሥራ ዕቅድ፤

ቀ) የመነሻ ካፒታሉን መጠንና ተሰብስቦ በባንክ ሂሳብ ገቢ መደረጉን ወይም ባንክ በሌለበት አካባቢ ከሆነ መዝጋቢው በወሰነው ቦታ መቀመጡን የሚያረጋግጥ ሰነድ፤

በ) ኀብረት ሥራ ማኀበሩ የሚሠራበት ቦታ ወይም ጽህፈት ቤት መግለጫ፤

14.2. አግባብ ያለው ባለሥልጣን የቀረበለትን የምዝገባ ማመልከቻ መርምሮ የተሟላ መሆኑን ሲያረጋግጥ በአምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ የኀብረት ሥራ ማህበሩን መዝግቦ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል። በዚህም የምዝገባ ምስክር ወረቀት ላይ ማኀበሩ በኀብረት ሥራ ማህበርነት የተመዘገበበት ቀን በመተዳደሪያ ደንቡ የመጨረሻው አንቀፅ ላይ ይጠቀሳል።

14.3. በኀብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ (4) መሰረት አግባብ ያለው ባለሥልጣን አመልካቹን ማህበር መመዝገብ አይገባውም ሲል የወሰነ እንደ ሆነ ምክንያቱን በጽሑፍ በማድረግ ለማህበሩ ወኪሎች በአምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ መግለፅ አለበት።

15. የዘር አምራች እና ግብይት ኅብረት ሥራ ማህበራት ካላቸው ልዩ ባህርይ የተነሳ በሚከተለው መልኩ ሊመዘገቡ ይችላል፡፡

15.1. በዘር አምራችና ግብይት ኅብረት ሥራ ማህበር ስም (as outgrower) ተመዝግቦ ምርቱን አምርቶ አባል ለሆነበትና አግባብነት ካለው የዘር ጥራት ተቆጣጣሪ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለተሰጠው ኅብረት ሥራ ዩኒየን የሚያቀርብ፤

15.2. በዘር አምራችና ግብይት ኅብረት ሥራ ማህበር ስም (as outgrower) ተመዝግቦ የማንም ኅብረት ስራ ዩኒየን አባል ሳይሆን ግን የሚያመርተው ጥሬ ዘር የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለተሰጠው የዘር ኩባንያ ወይም ኅብረት ሥራ ዩኒየን የሚያቀርብ፤

15.3. በዘር አምራችና ግብይት ኅብረት ሥራ ማህበር ተመዝግቦ ግን ዘሩን ራሱ አምርቶና አበጥሮ ለገበያ ለማቅረብ አግባብ ካለው የዘር ጥራት ተቆጣጣሪ ባለስልጣን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው፤

16. የኅብረት ሥራ ማህበራት የምዝገባ የምስክር ወረቀት የሚይዛቸው ዝርዝሮች፤

በፌዴራል ወይም በክልል የሚታተም የምዝባ መስክር ወረቀት የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡፡

17. የምዝገባ ቁጥር፣ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ስም፣ ሙሉ አድራሻ እና አርማ፣

17.1. የኅብረት ሥራ ማህበሩ የተመዘገበበት የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር፣ ቀን እና ዓመተ ምህረት ፣

17.2. የኅብረት ሥራ ማህበሩን የመዘገበው ባለሥልጣን ፊርማ፣

17.3. የመዝጋቢው ባለሥልጣን መ/ቤት ማህተም፣

17.4. የምስክር ወረቀቱ የተሰጠበት ቀን፣ ወር እና ዓመተ ምህረት፣

18. የምዝገባ ምስክር ወረቀት መስጠት ላይ የሚቀርብ ቅሬታ፤

በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ (5) መሰረት እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (6.4) መሠረት የአመልካች ወኪሎች በጽሁፍ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያላቸው ከሆነ፣ በክልል ሲሆን አግባብ ላለው የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም በፌዴራል ደረጃ ሲሆን ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በ60 ተከታታይ ቀናት ውስጥ አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ፡፡

19. የምዝገባ የምስክር ወረቀት ስለማገድ፤

19.1. በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ (9) መሠረት ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ከተቋቋመበት ዓላማና መርህ ውጪ ሲንቀሳቀስ ከተገኘ በዚህ ሕግ የተፈቀደለትን ሥራ እንዳይሠራ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ሊያግድ ይችላል፡፡

19.2. የታገደው ኅብረት ሥራ ማህበር ዕግዱ እንዲነሳለት በ30 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ካላመለከተ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ሕጋዊ የማፍረስ እርምጃ ይወስዳል፡፡

19.3. የታገደ ኅብረት ስራ ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ ዕግዱ እንዲነሳለት አግባብ ላለው ባለሥልጣን ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ጥያቄውን የተቀበለው አግባብ ያለው ባለሥልጣን የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ እግዱ እንዲነሳለት ያቀረበው ምክንያት በቂና አግባብ ሆኖ ሲገኝ እግዱን

ሊያነሳ ይችላል፡፡ አግባብ ያለው ባለሥልጣን እግዱን ያላነሳ እንደሆነ ያላነሳበትን ምክንያት በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡ አግባብ ያለው ባለሥልጣን በሰጠው ውሳኔ ያልተስማማ አካል የዳኝነት ሥልጣን ላለው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

20. የምትክ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ፤

20.1. የምትክ ምስክር ወረቀት ጥያቄ የሚቀርበው የምስክር ወረቀቱ ሲጠፋ፣ ሲበላሽ እና የስም ለውጥ ሲደረግ ይሆናል፡፡

20.2. የምትክ ምስክር ወረቀት ጥያቄ ሲቀርብ ከዚህ በታች ያሉት ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፡፡

20.2.1. የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ የጠፋ ስለመሆኑ በፍትህ አካላት ሲረጋገጥ፣ ወይም

20.2.2. የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ የተበላሸ ከሆነ እና የተበላሸው የምስክር ወረቀት አግባብ ላለው አካል ቀርቦ ሲረጋገጥ፣ ወይም

20.2.3. ምትክ የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ ጥያቄ ያቀረበው የኅብረት ሥራ ማህበር የስም ለውጥ ያደረገ ከሆነ እና የስም ለውጡ የተፈቀደበት የፍርድ ቤት ማስረጃ እና የኅብረት ሥራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የስም ለውጡን አስመልክቶ ያስተላለፈውን ውሳኔ እና የሥራ አመራር ኮሚቴ በደብዳቤ አረጋግጦ ማመልከቻ፤ ሲያቀርብ ነው፡፡

20.2.4. የስም ለወጡ ተቀባይነት የሚያገኘው የምትክ ምስክር ወረቀቱን ምዝገባ የሚያካሂደው አግባብ ያለው ባለሥልጣን የኅብረት ሥራ ማህበሩ ማህተም፤ መተዳደሪያ ደንብ፣ ሰነዶች እና ሌሎች የቀድሞ ስም ያለባቸው በሙሉ በአዲሱ ስም መለወጣቸውን ያረጋግጣል፤

20.2.5. የኅብረት ሥራ ማህበሩ ምትክ የምስክር ወረቀት ማግኘት የሚችለው አስፈላጊውን ክፍያ ፈጽሞ አግባብ ላለው ባለስልጣን ደረሰኝ ሲያቀርብ እና ቀደም ሲል በመዝገብ ላይ ባለው የቀድሞ ቁጥር ሲመዘግብ ነው፡፡

21. የጊዜያዊ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ እና አመላለስ

21.1. የጊዜያዊ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ

21.1.1. ጊዜያዊ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው ከአንድ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ብቻ ነው፡፡

21.1.2. የምስክር ወረቀት የሚሰጥባቸው ሁኔታዎች በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ 9 ከፊደል "ሀ" እስከ "ቀ" ድረስ የተዘረዘሩትን አሟልቶ ሲገኝ ሲሆን የጊዜያዊ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው ኅብረት ሥራ ማኅበሩ የሚሠራበት ቦታ

ወይም ጽህፈት ቤት መግለጫ እና በሌሎች መመሪያዎች የሚወሰኑ መግለጫዎችን ባያሟላም እስከሚያሟላ ድረስ ጊዜያዊ ምስክር ወረቀት ሊያገኝ ይችላል።

21.1.3. ጊዜያዊ ምስክር ወረቀት ያገኘ ኅብረት ሥራ ማህበር በተመዘገበበት የጊዜ ገደብ ውስጥ ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ያለው መብት እና ግዴታ ይኖረዋል።

21.2. የጊዜያዊ ምስክር ወረቀት አመላለስ

21.2.1. ኅብረት ሥራ ማህበሩ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ መስፈርቶችን ሙሉ ለሙሉ አሟልቶ ሲገኝ ጊዜያዊ የምስክር ወረቀቱን እንዲመልስ በማድረግ ተገቢውን ክፍያ ፈጽሞ አዲስ ቋሚ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል።

21.2.2. ኅብረት ሥራ ማህበሩ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ መስፈርቶቹን የማያሟላ ከሆነ በህጋዊ መንገድ ለማፍረስ በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 ከአንቀጽ 55 እስከ 60 በተደነገገው መሰረት አግባብ ባለው ባለሥልጣን የኅብረት ሥራ ማህበሩን የማፍረስ ተግባር ተፈፃሚ ይሆናል።

22. የምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለማሳደስ

22.1. ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር በየሦስት አመቱ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱን የማሳደስ ግዴታ አለበት።

22.2. የምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማሳደስ የሚከተሉት መሟላት አለባቸው።

22.2.1. ከቅርብ አደራጅ መ/ቤት ጉዳዩ ከሚመለከተው ክፍል ባለፉት ሦስት አመታት ኅብረት ማህበሩ በተቋቋመበት ዓላማ እና ተግባር እየሠራ ስለመሆኑ፣ የአባላት ተሳትፎ መኖሩን እና ለአባላት እየሰጠ ያለው አገልግሎትና ጥቅም አጭር መግለጫ እና ድጋፍ ለዚሁ ጉዳይ በተዘጋጀው ፎርም ላይ በመሙላት ያቀርባል።

22.2.2. በጠቅላላ ጉባኤ የፀደቀ የዘመኑ የኦዲት ሪፖርት፤

22.2.3. የብቃት ደረጃ ማረጋገጫና ዕውቅና ሠርተፊኬት፤

22.2.4. ቢያንስ ለሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት የሚያከናውናቸው የንግድ ሥራ ዕቅድ እና

22.2.5. ሌሎች በየጊዜው በሚወጡት የአሠራር መመሪያዎች ውስጥ የሚሰጡ መስፈርቶችን የሚያከብር መሆኑን የሚገልፅ ማስረጃ ማቅረብ አለበት።

22.2.6. የምዝገባ ምስክር ወረቀቱን ለማሳደስ ተገቢውን ክፍያ ይከፍላል፤

22.2.7. በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ቀርቦ የማያሳድስ የኅብረት ስራ ማህበር ግዴታውን ባለመወጣቱ አግባብ ባለው ባለስልጣን ከእንቅስቃሴ በደብዳቤ ይታገዳል።

22.2.8. በተወሰነው ጊዜ ውስጥ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱን ያላሳደሰ ኅብረት ሥራ ማህበር እንደታገደ የሚከተሉት እርምጃዎች ይወሰዳሉ።

ሀ) አግባብ ያለው ባለሥልጣን ኅብረት ሥራ ማህበሩ ያላሳደሰበትን ምክንያት በ3 ተከታታይ ቀን ውስጥ በጽሁፍ እንዲያቀርብ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ይሠጠዋል፡፡

ለ) በተወሰነው ጊዜ ውስጥ አጥጋቢ ምክንያት ካላቀረበ በሥራ አመራር ኮሚቴው አማካኝነት በ15 ቀን ውስጥ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲጠራ ይደረጋል፡፡

ሐ) የሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም ቦርድ ጠቅላላ ጉባኤውን ካልጠራ አግብባ ያለው ባለስልጣን ጠቅላላ ጉባኤውን በመጥራት ውሳኔ እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡

መ) አግባብ ያለው ባለስልጣን በህጉ እና በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ መሰረት ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፡፡

22.3. ከእገዳው በኋላ አግባብ ያለው ባለሥልጣን በሚያደረገው ማጣራት ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ካልኖረ በስተቀር በህጉ መሠረት ህልውናውን እንዲያጣ ይደረጋል፡፡

## ክፍል ፫

## የተመዘገበ የዘር አምራች እና ግብይት ኅብረት ሥራ ማህበር መብቶች

በዘር አምራች እና ግብይት ኅብረት ሥራ ማህበር መመዝገብ የሚያስገኘው ህጋዊ መብት

23. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አግኝቶ በኅብረት ሥራ አግባብ ያለው ባለስልጣን የተመዘገበ የዘር አምራችና ግብይት ኅብረት ሥራ ማሕበር በዕጽዋት ዘር አዋጅ ቁጥር 782/2005 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ ፫ መሰረት የተመዘገቡ ዝርያዎችን መነሻ ዘር ከሚያባዙ ተቋማት አራቢ ዘሮችን፣ ቅድመ መስራች ዘሮችን እና መስራች ዘሮችን ማግኘት ይችላል፤
24. በኅብረት ሥራ አዋጅ 985/2009 አንቀጽ 43 ንዑስ አንቀጽ ፩/ለ መሰረት የሚከተሉት ማለትም
    - 24.1. ለለመጋዝን ፣ ለጽህፈት ቤት፣ ለውስጥ ጥራት ቁጥጥር፣ለላቦራቶሪ፣ ለዘር ማበጠሪያ ግንባታና ሌሎች አገልግሎች
    - 24.2. ቅድመ መስራች እና መስራች ዘሮችን ለማባዛት፣ቴክኖሎጂ ለማስተዋወቅና ችግኞችን ለማዘጋጀት የሚውል መሬት በምድባ ያገኛሉ፡፡
    - 24.3. በኅብረት ሥራ አዋጅ 985/2009 አንቀጽ 43 አንቀጽ ፩/ ከ "ሀ" እስከ "መ" በተጠቀሰው መሰረት
        - 24.3.1. የስልጠና አገልግሎት
        - 24.3.2. የብድር አገልግሎት
        - 24.3.3. ከገቢ ግብር ነጻ የመሆን
        - 24.3.4. ከንብረት ጋር በተያያዘ ለሚነሳ ክርክር ከሚከፈል ዳኝነት ነጻ መሆንና
        - 24.3.5. ሌሎች ድጋፎችን


የማግኘት መብት አላቸው፡፡

25. ዘር ልዩ ጥንቃቄና አያያዝ የሚጠይቅ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በኅብረት ሥራ ማህበሩ ስም የተመዘገበና ከዘር ማምረት፣ዝግጅት፣ማጓጓዝና ማከማቸት ጋር ተያያዥ የሆኑ የኅብረት ስራ ማህበሩ ንብረቶች ያለ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ለሌላ ተግባር መዋል አይችሉም፡፡


## 26. <u>የኅብረት ሥራ ማህበራት አስተዳደራዊ መዋቅር፣</u>

26.1. የኅብረት ሥራ ማህበራት እንደተቋቋሙለት ዓላማ፣አይነት እና ባህሪያት የተለያየ አስተዳደራዊ የአደረጃጀት መዋቅር የሚኖራቸው ሲሆን ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ቢያንስ የሚከተለው መዋቅር ይኖረዋል፡፡

**ሀ) መሠረታዊ የዘር አምራቾች ኅብረት ሥራ ማህበራት ድርጅታዊ መዋቅር ሞዴል**



ለ) የዘር አምራቾች ኅብረት ሥራ ዩኒዩን ድርጅታዊ መዋቅር ሞዴል



26.2. ነማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር የሚኖው መዋቅራዊ አደረጃጀት፣ የእድገት ደረጃውን እና የስራ ባህሪውን ባገናዘበ መልኩ የሚደራጅ ሆኖ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፡፡

26.2.1. ጠቅላላ ጉባኤ፣

26.2.2. የሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም ቦርድ፣

26.2.3. የቁጥጥር ኮሚቴ፣

26.2.4. ሌሎች ንዑሳን ኮሚቴዎች፣

26.2.5. የቅጥር ሠራተኞች፡ ሥራአስኪያጅ፣ የእቅድና ፕሮጀክት፣የውስጥ ኦዲት፣የዘር ምርትና ግብይት ኃላፊና ባለሙያዎች (የዘር አግሮኖሚስቶች፣የላቦራቶሪ፣የግብይት)፤የሰውና የፋይናነስ አስተዳደር፣ የንብረት ግዥና አስተዳደር ሃላፊዎችና ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

## 27. <u>የኅብረት ሥራ ማህበራት የበጀት ዓመት</u>

27.1. ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር የበጀት አመት ይኖረዋል፡፡

27.2. የበጀት ዓመቱም የኅብረት ሥራ ማህበሩን ዓይነት እና ባህሪ የተከተለ ሆኖ በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ በጠቅላላ ጉባኤ የሚወሰን ይሆናል፡፡

### ክፍል ፮

### የዘር አምራች እና ግብይት ኅብረት ሥራ ማህበር ሃላፊነት፣ ተግባርና ግዴታ

### መሰረታዊ የዘር አምራች እና ግብይት ኅብረት ሥራ ማህበር  ተግባርና ሃላፊነት፣

28. የአባላት የፋይናንስ አቅም የሚያጎለብቱ አማራጭ የፋይናንስ ምንጭ የሚሆኑ ፕሮጀክቶችን በመንደፍ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል

29. የዘር ማምረት፣ዝግጅትና ግብይት ወቅታዊ ሥራ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ኅብረት ስራ ማህበሩ ያለውን ትራክተር፣ መውቂያ፣የዘር ማበጠሪያ እና የጭነት ተሽከርካሪ የኅብረት ስራ ማህበሩን ስራ ካጠናቀቁ በኂላ  በኅብረት ሥራ አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ ፩/መ መሰረት በእርሻ ሥራ ለተሰማሩ አርሶ አደሮቸ በተመጣጣኝ ክፍያ አገልግሎት መስጠት ይችላሉ፡፡

30. በተጠኑ የኢንቨስትመንት አይነቶች ላይ አባላቱ ፍላጎት እንዲያሳድሩ በማድረግ ተገቢ የብድር አቅርቦት እንዲያገኙ ያመቻቻል

31. አባላት በተሰማሩባቸው የዘር ምርትና ተያያዥነት ያላቸው የስራ ዘርፎች ውጤታማ መሆናቸውን በየጊዜው በባለሞያ እያስጠኑ ቀጣይ ድጋፍ ያደርጋል

32. በመተዳደርያ ደንቡ በሚወሰነው መሰረት ለአባላት ምርት የመጋዘንና የትርንስፖርት አገልግሎት ይሰጣል

33. አግባብ ከሆነ የዘር ጥራት ተቆጣጣሪ ባለስልጣን በሚሰጠው የጊዜ ሠሌዳ መሰረት የዘር ጥራት ቁጥጥር ሲካሄድ ተገቢውን ትብብር ያደርጋል፡

34. የውስጥ ጥራት ቁጥጥር አገልግሎት ለአባላቱ ይሰጣል፡፡

35. አባላት ያመረቱትን ዘር በገባው ውል መሰረት መረከብ እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 13.3 የተመዘገበ ኅብረት ሥራ ማህበር ከሆነ ማበጠር፣ማዘጋጀትና መሸጥ አለበት፡፡
36. ግዴታዎችን በተመለከተ በኅብረት ስራ አዋጅ ቁጥር 985/2009 እና ደንብ ቁጥር--------መሰረት ተፈጻሚ የሚደረግ ይሆናል፡፡

### የዘር አምራችና ግብይት የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን ተግባርና ሃላፊነት

በመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚከናወኑ የተግባር እና የኃላፊነት ድግግሞሽ ሳይኖር የዘር አምራችና ግብይት ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየን የሚከተሉት ተግባራት እና ኃላፊነቶች ይኖሯቸዋል፡፡

37. ከመሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት ምርትን በመረከብ እሴት በመጨመር በሀገር ውስጥ እና በሀገሪቱ የዘርና ተዛማጅ ህጎች መሰረት ከውጭ ገበያ በማስገባት ወይም በኮሚሽን የግብይት ስረዓት እና በሌሎች የግብይት ዓይነቶች አባላት የምርታቸው ትክክለኛ ዋጋ እንዲያገኙ ያደርጋሉ፣
38. አባል መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት በሰለጠነ የሰው ሀይል እንዲመሩ ተገቢውን ዕገዛ ያደርጋሉ፡፡
39. ከትምህርት ተቋማት፤ከምርምር እና ሌሎች መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመሆን የአባላትን የቴክኒክ ክህሎትና ችግር ፈቺ ምርምር ላይ ተቀናጅተው ይሰራሉ፡፡
40. የአባላትን የዘር ምርት ተደራሽነት እንዲኖረው ደረጃውን የጠበቀ የምርት መሸጫ ቅርጫፍ ማዕከላት ሊያቋቁሙ ይችላሉ፣
41. የኅብረት ሥራ ማህበራት ከአባላት የሰበሰቡትን ምርት እና ግብዓት የሚያስቀምጡበት ወይም የሚያከማቹበት የተለያየ አይነትና ደረጃ ያለው ዘመናዊ መጋዘን በራሳቸው እና ከሌሎች ድጋፍ ሰጪዎች ጋር ወጪን በመጋራት ሊገነቡ ይችላሉ፡፡
42. በመተዳደርያ ደንቡ በሚወሰነው መሰረት ለአባላት ምርት የመጋዘንና የትርንስፖርት አገልግሎት ይሰጣል
43. የመገልገያ መሰረተ ልማት ግንባታዎች የሚከናወኑት አባላትንና ተጠቃሚዎችን ማዕከል ያደረጉ እና በጠቅላላ ጉባኤ ፍላጎትና ውሳኔ መሠረት ይሆናል፡፡
44. ለአባል መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት እና ለራሳቸው ስራ የሚያገለግሉ የቴክኒክ መሳሪያዎች ወይም ማሽነሪዎች ግዢ በጨረታ ህግ ለማካሄድ የሚያስችል የስፔስፍኬሽን ዝግጅት እና በግዥ አፈፃፀም ላይ የባለሙያ ድጋፍ ያደርጋል፡፡
45. ከመሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት አቅም በላይ የሆኑትን የቴክኒክ መሳሪያዎች ወይም ማሽነሪዎች እንደ አስፈላጊነቱ የኪራይ አገልግሎት ይሰጣሉ፣

46. የአባላቱንና የኅብረት ስራ ዩኒየኑን ህልውና በዘላቂነት ለማስቀጠል በየጊዜው በደረሱበት የእድገት ደረጃ የተለያዩ አይነት የዘር ምርትና ግብይት እንዲሁም ከቋሚ ንብረቶች ጋር የተያያዙ መድን ዋስትናዎችን እንዲያገኙ ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡

47. የውስጥ የጥራት ቁጥጥር ስርአት ይዘረጋሉ፤

48. የመነሻ ዘር በማባዛት ወይም በመግዛት ለአባላት ያቀርባሉ፤

**የዘር አምራች እና ግብይት ኅብረት ሥራ ማህበር ግዴታዎች፤**

49. የኅብረት ሥራ ማህበራት የዕለት ተዕለት ስራቸውን ሲያከናውኑ መፈፀም የሚገባቸው ግዴታዎች በኅብረት ሥራ አዋጅ ቁጥር 985/2009 እና በደንብ ቁጥር …./2009 የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆኖ የሚከተሉትን ዝርዝር ግዴታዎች ያካትታል፡፡

49.1. የኅብረት ሥራ ማህበራት ዓላማና ተግባር መሰረት ያደረገ እና የአባላትን ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ችግሮችን የሚፈታና የዕለት ተዕለት ስራቸውን ለማከናወን የሚያስችላቸው የንግድ የሥራ ዕቅድ ያዘጋጃሉ፡፡

49.2. የኅብረት ሥራ ማህበራት ዕቅድ ቢያንስ የሚከተሉትን ዝርዝሮች ማካተት አለበት፡፡

49.2.1. የኅብረት ሥራ ማህበሩ ዕቅድ ማጠቃለያ፣

ሀ) መግቢያ፣

ለ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ስም፣

ሐ) የሚገኝበት አድራሻ፣

መ) ስለ ህጋዊ ሰውነቱ መግለጫ (ያገኘበት ዘመን፣ አይነቱ፣የሥራ ክልሉ እና የአባላት ሁኔታ፣ዕቅዱን ለመፈጸም ኢኮኖሚያዊ አቅሙ፣)

ሠ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ተልዕኮ፣ራዕይ እና እሴት፣

49.2.2. የዕቅዱ ዓላማ እና ግብ፣

ሀ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ፍላጎት፣ችግሮች እና ምቹ ሁኔታዎች፣

ለ) ያሉ ጠንካራ ጎኖች፣ደካማ ጎኖች፣ አጋጣሚዎች እና ሥጋቶች፣

ሐ) ከዕቅዱ የሚጠበቅ ውጤት፣

መ) ዝርዝር ተግባራት እና የአፈጻፀም ስልት፣

ሠ) የሚገኘውን ገቢ ፣ ወጪ እና ልዩነት (በብልጫ ወይም በማነስ)

ረ) ተግባራቱን ለማስፈጸም የፋይናንስ ምንጭ

49.3. የኅብረት ሥራ ማህበራት ስራቸውን ለማከናወን የሚረዳቸው ቢያንስ ዋና ዋና መዛግብቶች፣ ቅፆች፣ ፎርሞች፣ የሂሳብ መዛግብትና ሰነዶች ሚሟላት አለባቸው፡፡ እነዚህም፡-

49.3.1. መዛግብት

ሀ) የአባላት መዝገብ፣

ለ) የአባላት የተሳትፎ መዝገብ፣

ሐ) የጠቅላላ ጉባኤ ቃለ ጉባኤ መዝገብ፣

መ) የስራ አመራር ኮሚቴ/ ቦርድ ቃለ ጉባኤ መዝገብ፣

ሠ) የቁጥጥር ኮሚቴ ቃለ ጉባኤ መዝገብ፣

ረ) የብድር ኮሚቴ ቃለ ጉባኤ መዝገብ፣

ሰ) የግዢ ኮሚቴ ቃለ ጉባኤ መዝገብ፣

ሸ) የሺያጭ ኮሚቴ ቃለ ጉባኤ መዝገብ፣

ቀ) የቅጥር ኮሚቴ ቃለ ጉባኤ መዝገብ፣

በ) የቋሚ ንብረት መዝገብ፣ እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች መዛግብት

49.3.2. ልዩ ልዩ ቅጾች

ሀ) የአዲስ እና የእንደገና አባልነት ጥያቄ ማመልከቻ ቅፅ፣

ለ) የንብረት ገቢ ማድረጊያ ቅጽ፣

ሐ) የንብረት ወጪ መጠየቂያ ቅጽ፣

መ) የብድር ውል ቅጽ፣

ሠ) የተመን ቅጽ፣

49.3.3. ልዩ ልዩ ፎርሞች

ሀ) የንብረት ግዥ መጠየቂያ ፎርም፣

ለ) የብድር ማመልከቻ ፎርም፣

ሐ) የአዲስ አባላት ማመልከቻ ፎርም፣

መ) የእንደገና ተመላሽ አባላት ማመልከቻ ፎርም፣

ሠ) ከአባልነት አባላት ሲሰናበት የሚሟላ ፎርም፣

ረ) የወራሽ መሰየሚያ ፎርም፣

49.3.4. የሂሳብ መዛግብት እና ሰነዶች

49.3.4.1. የሂሳብ መዛግብት፣

ሀ) የገቢ መዝገብ፣

ለ) የወጪ መዝገብ፣

ሐ) ሌጀር፣

መ) የሂሳብ ማመዛዘኛ መዝገብ፣

ሠ) የጥሬ ገንዘብ መቆጣጠርያ መዝገብ፣

49.3.4.2. የሂሳብ ሰነዶች

ሀ) የገቢ ደረሰኝ፣

ለ) የወጪ ደረሰኝ፣

ሐ) የዕለት ሺያጭ ደረሰኝ፣

መ) የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ፣

ሠ) የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ፣

ረ) የደሞዝ መክፈያ ሰነድ፣

49.3.4.3. የሂሳብ ቅጾች

ሀ) የውሎ አበል መጠየቂያ እና ማወራረጃ ቅፆች፣

ለ) ሠነድ ለሌላቸው የገንዘብ መክፈያ ቅጽ

ሐ) የቅድሚያ ወጪ መጠየቅያ ቅጽ፣

49.4. ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር በየዓመቱ ከሚያከፋፍለው የተጣራ ትርፍ ውስጥ በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሠረት 3 ከመቶ ለኅብረት ስራ ፈንድ ማዋል አለበት፡፡

49.5. ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር በየዓመቱ ለኅብረት ሥራ ፈንድ ከሚያጠራቅመው ውስጥ ግማሹን ወይም 50 ከመቶ በየዓመቱ እየቀነሰ በሊጉ ስር ለተቋቋመው የኅብረት ሥራ ፈንድ አካል በቀጥታ ወይም በኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየኑ ወይም በኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽኑ አማካኝነት ያስተላልፋል፡፡

49.6. ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን በሥሩ ከታቀፉ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ከተጣራ ትርፍ የተሰበሰበውን የኅብረት ሥራ ፈንድ እና በዚህ አንቀጽ 26.5. መሰረት በየዓመቱ ከተገኘው የተጣራ ትርፍ ላይ ቀንሶ በሊጉ ስር ለተቋቋመው የኅብረት ሥራ ፈንድ አካል በቀጥታ ወይም በኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን አማካኝነት የሚያስተላልፍ ይሆናል፡፡

49.7. የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን በሥሩ ከታቀፉ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየኖች ከተጣራ ትርፍ የተሰበሰበውን የኅብረት ሥራ ፈንድ እና በዚህ አንቀጽ 26.5. መሰረት በየዓመቱ ከተገኘው የተጣራ ትርፍ ላይ ቀንሶ በሊጉ ስር ለተቋቋመው የኅብረት ሥራ ፈንድ አካል በቀጥታ የሚያስተላልፍ ይሆናል፡፡

49.8. የኅብረት ሥራ ማህበራት ጥራት ያለው ምርት እና አገልግሎት ለአባላቱ በወቅቱ ማቅረብ አለበት፣

49.9. የኅብረት ስራ ማህበራት ከአባላት የሚሰበስቡትን ምርትም እና ለአባላት የሚያቀርቡትን የግብዓት ወይም የፍጆታ እቃዎች አቅርቦት የሚከተሉትን የምርት ጥራት መጠበቂያ መሣሪያዎችንና መገልገያዎችን አሟልተው መገኘት አለባቸው፡፡

እነዚህም፤

ሀ) ደረጃቸውን የጠበቁ ንፁህ የማከማቻ መጋዘኖች፣

ለ) ንፁህ የመያዣ እቃዎች እና ማሸጊያዎች፣

ሐ) ዘመናዊ የማበጠሪያ መሳሪያዎች፣

መ) የተመረጡ ሰብሎችን የማከሚያ /ፉሚጌሽን/ አገልግሎት የሚሰጡ ቁሳቁሶች፣

ሠ) የምርት ጥራት ደረጃ መጠበቂያ መሣሪያዎች፣

ረ) የስም እና ምልክት መለጠፊያ ወይም የሌብል ማድሪያ ቁሳቁስ፣

ረ) የመጋዘን መቆጣጠሪያ ቢን ካርድ እና ስቶክ ካርድ፣

49.10. የኅብረት ሥራ ማህበራት ከአባላት የሚሰበስቡትን ምርት አያያዙን በማሻሻል የምርቱን ወይም የአገልግሎቱን አቀራረብ ለተጠቃሚው ተደራሽ ማድረግ፣

49.11. ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ለተጠቃሚው ምቹ እንዲሆን ለማድረግ በሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች ውስጥ ማለፍ አለባቸው፣

49.11.1. የአባላት እና የተጠቃሚ ፍላጎትን መሠረት ያደረገ እንዲሆን የምርቱን መጠን፣ ዓይነት፣ ቅርፅ፣ አያያዝ ለአገር ውስጥ እና ለውጭ ገበያ በሚሆን መልኩ ማዘጋጀት ወይም ማቀናበር፣

49.11.2. የአባላት እና የተጠቃሚ ፍላጎትን ታሳቢ ያደረገ የአገልግሎቱን አሰጣጥ ወቅታዊ እና አቀራረቡ ቀልጣፋ እና ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ፣

## ክፍል ፳

## የባለድርሻ አካላት ሃላፊነትና ተግባር

50. የፌደራልና የክልል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲዎች በማቋቋሚያ አዋጅ በተሰጣቸው ስልጣንና ተግባር መሰረት ለዘር አምራችና ግብይት የኅብረት ሥራ ማህበራት
    50.1. የማደራጀት፣ የኦዲት ፣የህግ ድጋፍ፣የምክር እና ኢንስፐክሽን አገልግሎት ይሰጣል
    50.2. ለዘር ማሰባሰብና ተጓዳኝ ሥራዎች አስፈላጊውን ብድር እንዲያገኙ ያመቻቻል፤
    50.3. ለልዩ ልዩ ግንባታ ተግባር የሚውል መሬት አንዲያገኙ ያመቻቻል
    50.4. የገበያ መረጃ መስጠትና ትስስር ለመፍጠር ድጋፍ ያደርጋሉ፤
    50.5. የፋይናንስ ችግሮቻቸውን ለመቅረፍ ከቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት በቅንጅት እንዲሰሩ ያመቻቻል፤
51. የፌደራል እርሻና ተፈጥሮ ሃብት ሚኒስቴር እና የክልል ቢሮዎች
    51.1. የዘር አምራች ኅብረት ሥራ ስራዎችን በበላይነት የሚያስተባብር አካል ያቋቁማሉ።
    51.2. ክትትልና የሙያ ድጋፍ የሚያደርግ ባለሙያ/ባለሙያዎች በቋሚነት ይመድባሉ።
    51.3. የመነሻ ዘር አቅርቦትን ያመቻቻሉ።
    51.4. ለመነሻ ዘር ብዜት የሚሆን የገጠር መሬት ያመቻቻሉ
    51.5. የባለድርሻ አካላትን በማስተባበር የብድር፣ የመጋዘን፣ የማበጠሪያ ማሽኖችና የሌሎች ቁሳቁሶች ችግሮች እንዲፈቱ አስፈላጊውን ድጋፍ ሁሉ ያደርጋሉ
    51.6. የኅብረት ሥራ ማህበራት የገበያ አማራጮችን እንዲያሰፉ ያግዛሉ፡፤
    51.7. ከአጋር አካላት የሚቀርቡ ድጋፎችን አቀናጅተውይመራሉ።

51.8. ውልን መሰረት ያደረገ የመነሻ ዘር ብዜት የወደፊቱ አቅጣጫ ቢሆንም ይህ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እስከሚሆን አሁን እየተሠራበት ያለው የመነሻ ዘር ድልድል ሥርዓት የዘር አምራች ኅብረት ሥራ ማህበራትን ያገናዘበ መሆን አለበት።

51.8.1. የክልል ግብርና ቢሮዎች የዘር አባዥ ኅብረት ሥራ ማህበራትን የመነሻ ዘር ፍላጎት ያጠናቅራሉ፣ የቀረበላቸውን መነሻ ዘር በፍትሀዊነት ይደለድላሉ።

51.8.2. የዘር ብዜት ኅብረት ሥራ ማህበራት የጠየቁትን ዘር ማግኘታቸውን ተከታትለው ያስፈጽማሉ።

51.9. የአደጋ ጊዜ ዘር አቅርቦትና ሥርጭት ወቅት የኅብረት ማሕበራትን በሚጎዳ መልኩ እንዳይሆን አስፈላጊውን ጥንቃቃና ክትትል ያደርጋል።

52. የፌደራል እና የክልል ምርምር ተቋማት

52.1. በውል ላይ የተመሰረተየመነሻ ዘር አቅርቦት ሥራ ይሰራሉ።

52.2. ከኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር በመቀናጀት አዳዲስ ዝርያዎች እንዲተዋወቁና በቅድመ እና መስራች ዘር ብዜት ላይ የሙያ ድጋፍ ይሰጣሉ፤በኮንትራት አራቢ ዘር ማባዛት ይችላሉ።

52.3. ከመደበኛው የመነሻ ዘር ሥርጭት ስርዓት ውጭ የሚደረገውን የመነሻ ዘር ስርጭት መልክ ለማስያዝ ይቻል ዘንድ፡

52.3.1. ከምርምር ማዕከላትና ሌሎች መነሻ ዘር ምንጮች መደበኛ ባልሆነ መልኩ የተሸጠ ዘር መረጃ ለክልል ግብርና ቢሮ በአካባቢያቸው ለሚገኙ የግብርና ቢሮዎች ዘሩ ከመሰራጨቱ በፊት ሪፖርት ያደርጋሉ።

52.3.2. የክልል ግብርና ቢሮዎች ከምርምር ማዕከላት ያሚገኙትን መረጃ መነሻ በማድረግ የዘር ፈቃድ ላላቸው የዘር አባዥ ኅብረት ሥራ ማህበራት ወይም በኮንትራት ለሚያመርቱ አካላት ብቻ እንዲያሰራጭ ክትትል ያደርጋሉ።

52.3.3. ሆኖም ግን፣ ጠንካራ ማህበራት በሌሉበት አካባቢና እንዲሁም በመደበኛውና በተሸሽጋገሪ የዘር ስርዓት በማይሸፈኑ ሰብሎች በግብርና ቢሮ እውቅና መነሻ ዘሮች ክልሉ የሚያውቀው የልማት ፕሮግራም ባላቸው አካላት ለኢመደበኛ ዘር የዘር ልማት እንዲሰራጭ ያደርጋል።

53. በዘር ጥራት ቁጥጥር አግባብነት ያላቸው የክልል ባለስልጣናት

53.1. በዕጽዋት ዘር አዋጅና ይህን ተከትለው በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት መስፈርቱን ላሟሉ የኅብረት ሥራ ዩኒየኖችና መሰረታዊ ኅብረት ስራ ማህበራት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣሉ፤

53.2. የዘር ጥራት በማረጋገጥ ሂደት የኅብረት ሥራ ማህበራቱ የሙያ አቅም እንዲገነቡ የስልጠና ድጋፍ ይሰጣሉ።

53.3. ድጋፍ ተኮር የሆነ የመስክ ጥራት ቁጥጥር እና ክትትል አገልግሎት ይሰጣሉ፤

53.4. በላብራቶሪ ደረጃ የዘር ጥራት ቁጥጥር አገልግሎት ይሰጣሉ ውጤቱም በወቅቱ ያሳውቃሉ።

54. መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች

54.1. ለኅብረት ሥራ ማህበራቱ የሚደረጉ ድጋፎች የማህበራቱን ዘላቂነትና በሚያረጋግጥ መልኩ እንዲሆን ይሰራሉ፤

54.2. ለኅብረት ስራ ማህበራት የሚሰጡ ድጋፎች (የግንባታ፣የማሽነሪዎች፣የዘር የመሳሳሉት) በህግ የተቀመጡ የአገሪቱን ደረጃዎች ያሚሉ መሆን አለበት።

54.3. የዘር አቅርቦትና ሥርጭትን በተመለከተ ድጋፍ ሲሰጡ የሚመለከተው የመንግስት መስሪያ ቤት እውቅናና በሚያወጣው ፕሮግራም መሰረት ተባብረው ይሰራሉ።

ክፍል ፱

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**55.** ሪፖርት አቀራረብ፡

የዘር አምራችና ግብይት የኅብረት ሥራ ማህበራት አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴን አስመልክቶ መረጃ ሲጠየቁ አግባብ ላለው ባለስልጣን ሪፖርት የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

56. አለመግባባት ስለሚወገድበት ሁኔታ፤

በዚህ መመሪያ አፈጻጸም ላይ አለመግባባት ሲያጋጥም በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009እና በዕጽዋት ዘር አዋጅ 782/2005 መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ ሆኖም በሚሰጠዉ ዉሳኔ ያልተስማማ ወገን ጉዳዩን አግባብ ላለዉ የፍትህ አካል የማቅረብ መብቱ የተጠበቀ ነዉ፡፡

57. የመተባበር ግዴታ፣

ማንኛዉም ሰዉ ይህን መመሪያ ለማስፈጸም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

58. ስለ መመሪያው መሻሻል፤

ይህ መመሪያ እንደ አስፈላጊነቱ ሊሻሻል ይችላል፡፡

59. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ …. ቀን ታህሳስ 2009 ዓ/ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ፪ሺ፱ ዓ/ም

ኡስማን ሱሩር ሲራጅ

የፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር